ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መለዕክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር አራት የካቲት 2012 ዓ/ም

## ከፍ ያለ ስም

ህልም አለኝ (I have a dream)

## ሰዋዊ

‹‹አዲሶቹ ፋሺስቶች››

## ቀለም

ወርሀ የካቲት ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው

# "ሕልም አለኝ"



# ርእሰ አንቀጽ

ኢሰመጉ

# ሊመጣ ያለው ጥፋት ያሠጋናል!

ያሳለፍነው የካቲት ወር በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጣቸው ዐበይት ጉዳዮች የተፈጸሙበት ነው፡፡ ከታሪካዊ ክስተቶቹ ብዙዎቹም ከሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው በመሆኑ ነው የዚህን ዕትም ይዘት ከዚያ አኳያ የቃኘነው፡፡ የካቲት 12 ቀን 1929ዓ.ም በፋሺስቶች የተፈጸመውን ጭፍጨፋ የሚዘክር፣ የጥቁሮችን የነጻነት ተጋድሎ የሚያወሳ እንዲሁም የፋሺዝም ፖሊቲካዊ እንቅስቃሴ አነሣሥና ውድቀት እንዲሁም አሁን በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኘው «አዲሱ ፋሺዝም» የተዳሰሰበት ጽሑፎች በ«ዲጂታል ጋዜጣችን» አዘጋጅች ቀርበዋል፡ ፡ በተጠቀሱት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ለማተኮር የወሰንነው ጉዳዮቹን እንዲሁ ከታሪካዊነታቸው አንፃር ብቻ ለመመልከት በማሰብ ሳይሆን ይልቁንም ዛሬም የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በዚያ ዐውድ ተረድተን ለማሳሰብ ነው፡፡

በዚህ ርእሰ አንቀጽ አርእስት «ሊመጣ ያለው ጥፋት ያሠጋናል!» ያልነውም ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ በውስጣችን መልካም ተስፋ ፈጥሮብን የነበረውንና ብዙ መሥዕትነት ተከፍሎበት ለፖሊቲካዊ ለውጥ መንሥዔ የሆነውን የነጻነት ትግል መጥፎ አቅጣጫ የሚያስይዝ፣ የካቲት 12 ቀን ከተፈጸመውም የባሰ የሕዝብ ዕልቂት ሊያስከትል የሚችል አዲስ ፋሺስታዊ አዝማሚያ በኢትዮጵያ ፖሊቲካ ውስጥ እየተስተዋለ ነው፡፡

የአስተሳሰብ አድማስ በሰፋበት 21ኛው ክ/ዘመን የአገራችን አክራሪ ብሔርተኛ ፖሊተከኞች ለተከታዮቻቸው የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች ‹ናትሲዎች›

በ፲፱ኛው ክ/ዘመን ሳይንሳዊ ሐቅንና የተፈጥሮ እውነታን በመፃረር ያቀነቅኑት የነበረውን «የዘር ማጥራት ዕሣቤ» እውን ለማድረግ ያስተላልፉ ከነበረው የዘር ፍጅት ጥሪ ጋር ተመሳሳይነቱ ሊያስደነግጠን ይገባል፡፡

በየአካባቢው የሚገኙ አክራሪ ብሔርተኛ ፖሊቲከኞች በቀሰቀሷቸው ግጭቶች ምክንያት በርካታ ኢትዮጵያውያን ተገድለዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል እንዲሁም በገዛ ሐገራቸው ተፈናቃይ ስደተኞች ሆነዋል፡፡ ራቅ ባለው ዘመን በአውሮፓ የተፈጸመውን የዘር ፍጅት ከራሳችን ዐውድ አኳያ ለመረዳት ቢከብደን በእኛው ዘመን በሩዋንዳ የተፈጸመው አካሄዳችንን ቆም ብለን እንድናስተውል ማንቂያ ሊሆነን በተገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ከታሪክ ባለመማራችን በዚያች አገር የተፈጸመውን ጭፍጨፋ ተከትሎ በሰላም አስከባሪነት ሠራዊት አሠማርታ በነበረችው ኢትዮጵያ ዛሬ በፖለቲከኞች ቅስቀሳ ምክንያት በብሔሮች መካከል የሚፈጠሩ ግጭቶች ተካርረው በመጨረሻ የዘር ፍጅት እንዳይፈጸምባት ያሠጋናል፡፡

«እንወክለዋለን» ለሚሉት ወገን የአንድ አካባቢ «ባለቤትነትን ከማረጋገጥ» ያለፈ የረባ መታገያ አጀንዳ የሌላቸው፣ በሁሉም ክልሎች የሚንቀሳቀሱ አክራሪ ብሔርተኛ ፖሊቲከኞች በቀላሉ እውን የሚሆን የሚመስል ከንቱ ተስፋ በመስጠት የብዙኃንን ድጋፍ አግኝተው ሥልጣን ለመያዝ ተዘጋጅተዋል፡፡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተወዳድሮ የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የዜጎች መብት ቢሆንም አካሄዱ ግን ሕጋዊ መሆን እንዳለበት እናምናለን፡፡ ስለሆነም፣ በዓመቱ መጨረሻ ላይ እንደሚካሄድ በሚጠበቀው አገር አቀፍ ምርጫ ለመሳተፍ በዝግጅት ላይ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተቋም ደረጃ፤ አባሎቻቸውም በግለሰብ ደረጃ ለደጋፊዎቻቸው የሚያስተላልፏቸው መልዕክቶች የሕግ ተጠያቂነት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ባለመዘንጋት የዘር ፍጅት ሊያስከትሉ የሚችሉ አደገኛ ጥሪዎችን ከማስተላለፍ እንዲታቀቡ በዚህኛው ዕትም እናሳስባለን፡፡

## የኀዘን መግለጫ

በ ኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ከ 15 ዓመታት በላይ ሲያገለግሉ የነበሩት ባልደረባችን አቶ በፍቃዱ ዋቅጅራ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው የተሰማንን ጥልቅ ኀዘን በዝግጅት ክፍሉ ስም እንገልጻለን።




## መልእክተ ኢሰመጉ

**አሳታሚ**

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

**የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች**

ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org


ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

# እፍታ

## ዜና




ገላውዲዮስ ግሩም

# የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በ እምነት ተቋማት ላይ እና አማኞች ላይ የሚደርሰውን ጥቃት አወገዘ

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ በ ቀን 04/7/2012 ዓ/ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ መንግስት የዜጎችን የሃይማኖት ነጻነት የማስከበር እንዲሁም የአምልኮ ስፍራዎችን ከጥፋት የመጠበቅ ግዴታውን በአግባቡ ይወጣ ዘንድ ጠይቋል።

ኢሰመጉ ባለፈው ሳምንት በአማራ ክልል እነዋሪ ከተማ በሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን ላይ የተፈጸመውን ቃጠሎ እና ንብረት ዘረፋ ተከትሎ ባወጣው መግለጫ እንደገለጸው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ቦታዎች የሚስተዋሉ በተደራጁ ሃይሎች በእምነት ተቋማት ላይ የሚደርስ ጥቃት ለማቆም መንግስት ሀላፊነቱን እንዲወጣ አሳስቧል።

# “ሰዋዊ”

# ‹‹አዲሶቹ ፋሺስቶች››

በሱራፍኤል ግርማ

የካቲት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ግራዚያኒ ላይ በምብ ተወርውሮ በመቁሰሉ ምክንያት ፋሺስቱ ወራሪ በኢትዮጵያውያን ላይ በፈጸመው ጭፍጨፋ የተገደሉ ሠማዕታትን ለማሰብ በየዓመቱ ዕለቱን እንዘክራለን፡፡ ዛሬ ያለንበትን ሁኔታ ለመረዳት ትናንት ያለፍንበትን ማስታወስ ተገቢ ነውና የፋሺዝም ሠለባ ሆና አምስት ዓመታትን በሠቆቃ ያሳለፈችው ኢትዮጵያ ከሰማንያ ዘመን በኋላ በገዛ ልጆቿ ወደ ፋሺዝም ሊወስድ የሚችለውን አስፈሪ ጎዳና እንዴት እንደተያያዘችው ከርዕዮተ ዓለሙ ታሪካዊ ዳራ በመነሣት ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

## ፋሺዝም ምንድር ነው?

የፋሺዝም ርእዮተ ዓለም በ1920ዎቹ የመጀመሪያዎቹ ዐሥርት ዓመታት በአውሮፓ ተፈጥሮ የነበረው አስከፊ የኢኮኖሚ መቃወስ እና የሀብት ኢ-ፍትሐዊ ክፍፍል የፈጠረውን የሕዝቦች ቅራኔ በመጠቀም ‹‹አዲስ መፍትሔ ይዘን መጥተናል!›› ባሉ ፖለቲከኞች አማካይነት ነበር የገነነው፡፡ ከእነዚያ ፖለቲከኞች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱት የኢጣሊያው ቤኒቶ ሙሶሊኒ እና የጀርመኑ አዶልፍ ሒትለር ናቸው፡፡

ቤኒቶ ሙሶሊኒ ‹ብሔራዊ የፋሺስት ፓርቲ› በተባለ ድርጅቱ አማካይነት በኢጣሊያ ተፈጥሮ የነበረውን የተቋማት፣ የፓርቲዎች እንዲሁም የልሒቃን መሸመድመድ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም የ‹‹ብሔራዊ›› እና ‹‹ማኅበራዊ›› ፖሊሲዎች ቅይጥ የሆነ መፍትሔ ይዞ ወደ ፊት ወጣ፡፡ ፋሺስቶች ‹‹ወገናችን›› የሚሉትን ሕዝብ ቀልብ ለመማረክ ሲሉ ሕዝቡን አንድ እንደሚያደርጉ፣ ከማንኛውም ሌላ ቡድን ይልቅ የእርሱን ጥቅም በቅድሚያ እንደሚያስከብሩ ሰብከዋል፡፡ የፋሺስት ፓርቲ መሥራች የሆነው ሙሶሊኒ ‹‹ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ›› የተባለ የጦር ሠራዊት አስተኔ ቡድን በማቋቋም የፖሊቲካ ተቀናቃኞቹን በማሸበርና ተጽእኖ በመፍጠር ነበር ወደ ሥልጣን ለመውጣት የቻለው፡፡

በጀርመንም ‹‹ናትሲዝም›› ተብሎ የሚታወቀውን የፋሺዝም መንታ ርእዮተ ዓለም የሚያቀነቅኑ አክራሪ ብሔርተኞች ወደ ሥልጣን ለመውጣት የቻሉት በአገሪቱ ተፈጥሮ የነበረውን አስከፊ የኢኮኖሚ ድቅቀት እንደሚቀርፉ፣ የሕዝቡን ጥቅም እንደሚያስከብሩ በመቀስቀስ ነበር፡፡ በሂትለር የሚመሩት የጀርመን አክራሪ ብሔርተኞች የጀርመን ሕዝብን ጥቅም እንደሚያስከብሩ ቃል ቢገቡም በእነርሱ ዘንድ ‹‹ሕዝብ›› የሚለው ዕሣቤ አይሁዳውያንና ሌሎች ‹‹የማይፈለጉ›› ተብለው የተፈረጁ ቡድኖችን የሚያጠቃልል አልነበረም፡፡ የአገራቸውን ክብርና የጀርመን ዘርን ልዕልና እንደሚያድሱ የነዙት ስብከት ሰፊ ተቀባይ በማግኘቱ እ.አ.አ በ1932ዓ.ም በተካሄደው ምርጫ አሸናፊዎች በመሆን የሕግ ማውጫ ምክር ቤቱን ለመቆጣጠር ቀስ በቀስም ሥልጣን ጠቅልለው ለመያዝ አስችሏቸዋል፡፡

ዳሩ ግን በአክራሪ ብሔርተኛነት ላይ የተመሠረተው የፋሺዝም (ናትሲዝም) የመጨረሻ ግቡ በሌሎች ኪሣራ የራስን ጥቅም ማስከበር በመሆኑ አሠቃቂ የዘር ፍጅት አስከትሏል፤ በመላው አውሮፓ፣ በእስያና በአፍሪካ ከባድ ውድመት ላደረሰው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መንሥዔ ሆኗል፡፡ በጦርነቱ የመጨረሻ ውጤትም የአክራሪ ብሔርተኞቹ ሽንፈት ሆኖ ሂትለርና ሙሶሊኒ በለኮሱት እሳት ተቃጥለው ጠፍተዋል፡፡

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል ግን የፋሺዝም እንቅስቃሴውን ሙሉ በሙሉ አላጠፋውም፡፡ ‹‹ኒዮ-ፋሺዝም›› በሚል ሥያሜ እንደ አዲስ አውሮፓ ውስጥ በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኘው አክራሪ ብሔርተኛነት ከመገለጫዎቹ መካከል ዋነኛው ስደተኞችን የጥቃት ዒላማ ማድረግና ‹የዘር ንጽሕና ማስጠበቅን› መስበክ ነው፡፡

ሌላው የአክራሪ ብሔርተኛነት መገለጫ በአንድ ሥፍራ የሚኖሩ ሰብዓዊ ፍጡራንን ‹‹መጤ›› እና ‹‹ተወላጅ›› በሚሉ መደቦች ከፍሎ መመልከትና የዜጎችን በመረጡት የሐገራቸው አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት ነጻነት መገደብ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ራሳቸውን የአንድ ሥፍራ ‹‹ልዩ ባለቤቶች›› አድርገው የሚቆጥሩ አክራሪ ብሔርተኞች ‹‹መጤ›› ብለው በሚጠሯቸው ዜጎች ላይ የሚያደርሱትን ጫና እንዲሁም የሚፈጽሟቸውን ጥቃቶች እንደ ዐርበኛነት የመውሰድ አዝማሚያ ይስተዋልባቸዋል፡፡

የቀዳሚዎቹ ፋሺስቶችም ሆኑ ዘመነኞቹ አክራሪ ብሔርተኞች እውነተኛ ዓላማ የጅምላ ፍጅት በመፈጸምም ቢሆን የራሳቸውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስከበር ነው፡፡ ተከታዮቻቸውን ለጥፋት የሚያነሣሡትም ‹‹ባዕዳን›› ከሌላ ሥፍራ መጥተው የተፈጥሮ ሀብቶችንና የሥራ ዕድሎችን መቀራመታቸውን በመስበክ ነው፡፡ ዳሩ ግን ይህን ዓላማቸውን ለመሸፈን ‹‹መጤዎች›› በንዑሥ ማኅበረሰብ ራሳቸውን ነጥለው ስለሚኖሩ የአገሬውን ቋንቋ ለመልመድ እንኳ ፈቃደኞች እንደማይሆኑ፣ በከተሞች ደግሞ የቁጥርም ብልጫ ስለሚኖራቸው ነባሩን ልማድና ወግ ‹‹ባዕድ›› በሆነው የራሳቸው ባሕል እንደሚተኩ ይሰብካሉ፡፡

እነዚህን ሁሉ ምልክቶች በአገራችን የፖሊቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ እያስተዋልን ነው፡፡ ብሔርተኛ ፖሊቲከኞች ባሕልንና ቋንቋን በማስጠበቅ ሽፋን ‹‹የእኛ ነው›› የሚሉት ወገን ተወላጆች ከሌላ ብሔር ተወላጆች ጋር ጋብቻ እንዳይፈጽሙ፣ ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ሰው ጋር ግብይት እንዳይፈጽሙ ቅስቀሳ ሲያደርጉ መሰንበታቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በእርግጥም ቅስቀሳቸው ተቀባይ አግኝቶ የብዙዎች ትዳር ፈርሷል፤ የሸቀጥ ልውውጥ ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ መስተጋብርም ጭምር የሚካሄድባቸው የገበያ ሥፍራዎች በብሔር ድንበር ተበጅቶላቸው ‹‹የእገሌ ብሔር ተወላጅ እዚህ መገበያየት አይችልም›› ከሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

የዚህ ዓይነቱ አክራሪ ብሔርተኛነት መጨረሻው ምን እንደሚሆን ታሪክ በግልጽ ስለሚያሳየን ማዕበሉን ማስቆም በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም፣ አክራሪ ብሔርተኛነት ፋሺስታዊ ጥፋት ሊያስከትል እንደሚችል በመገንዘብ ልንፈጥር የምናልመው ማኅበረሰብ በሰብዓዊ ክብር፣ ነጻነት፣ ዴሞክራሲና እኩልነት መርሖዎች ላይ የተመሠረተ እንዲሁም ብዝኃነት፣ መቻቻል፣ ፍትሕ፣ የወንድማማችነት መንፈስ የነገሠበት ሊሆን ይገባል፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።



# ከፍ ያለ ስም !

ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒዮር (Dr. Martin Luther King Jr.) (1921-1960 ዓም)

## “ሕልም አለኝ”

ገላውዲዮስ ግሩም

ያሳለፍነው የፈረንጆች ወር (ፌብሩዋሪ) የጥቁር ታሪክ ወር” (black history month) በመባል የሚታወቅ አሜሪካ ውስጥ አመታዊ የመታሰቢያ በዓል ሲሆን የአፍሪካ-አሜሪካዊ የታሪክ ወር በመባልም ይታወቃል ፡፡ በዓሉ በአሜሪካ እና በካናዳ ካሉ መንግስታት በይፋ እውቅና ያገኘ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ በአየርላንድ ፣ በኔዘርላንድ እና በዩናይትድ ኪንግደም በይፋ እንዲከበር ተወስኗል፡፡ በአፍሪካ ዲያስፖራዎች ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ሰዎችን እና ክስተቶችን ለመዘከር እና ስራቸውን ለማስታወስ ታቅዶ እሚከበር በዓል ነው ፡፡ በአሜሪካ እና በካናዳ ፌብሩዋሪ ውስጥ ይከበራል ፣ በአየርላንድ ፣ ኔዘርላንድስ እና እንግሊዝ ውስጥ ኦክቶበር ወር ላይ ይከበራል።

ታዲያ ዛሬ አለም ላይ የጥቁሮች ነጻነትን ስናወሳ ስሙን እማንዘነጋው በጥቁሮች ታሪክ ወር በዓልም ሳማቸው በመሪነት የሚነሳውን ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁነየርን እና ታዋቂውን ህልም አልኝ ንግግራቸውን በከፍ ያለ ስም አምዳችን ልናነሳ ወደናል።

መልካም ቆይታ

ማርቲን ሉተር ኪንግ የተወለዱት በሀገረ አሜሪካ ጥቁሮች ከነጮች እኩል መብት ያልነበራችው ሀሳባቸውን እና አላማቸውን ለማከናዎን እማይችሉበት ፣በዘረኝነት በታመሱበት ወቅት እ.ኤ.አ በወርሀ ጥር በ 15ኛው ቀን 1929 ነው።

በቀደመው ዘመን አፍሪካ አሜሪካውያን ከባርነት ቢላቀቁም በዘር ላይ ከተመሰረተው ዓይነተ ብዙ መድልዎና ጭቆና ነፃ ለመውጣት እልህ አስጨራሽ ትግልን ጠይቋቸዋል፡፡

በዚያን ጊዜ በአሜሪካ አፍሪካ አሜሪካውያኑ ተመርጠውና ተሾመው ለከፍተኛ ኃላፊነት ለመብቃት ይቅርና መሠረታዊ የመምረጥ መብታቸው በሰፊው ይጣስና ይጨፈለቅ ነበር፡፡

በ21 ግዛቶች ከነጭ ጋር መጋባት የሚከለክሉ ሕጐች ስራ ላይ ውለው የነበረ መሆኑ የመድልዎው አንድ ገፅታ ሆኖ ይነሳል፡፡

በ2ኛ ደረጃ ዜግነት ከመታየታቸውም በላይ ይፈፀሙባቸው የነበሩ መድልዎች ሰብዕናቸውን የሚፈታተኑ ነበሩ፡፡

አፍሪካ አሜሪካውያኑ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በስነ-ልቦና ይፈፀምባቸው የነበረው ማግለልና ይደርስባቸው የነበረውን ፖለቲካዊ ጭቆና ለማስወገድ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት የዘለቀ ትግልና ሙግት አድርገዋል፡፡

የአፍሪካ አሜሪካውያኑን ሁለገብ የመብትና የእኩልነት ትግል ፈር በማስያዝ የመሪነት ሚና ከተጫወቱት መካከል ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር አንዱ ናቸው፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር በ1963 እ.ኤ.አ. በዋሽንግተን ዲሲ አደባባይ ለተሰበሰቡት አድማጮቹ በሰው ልጅ የነፃነትና የእኩልነት ታሪክ ውስጥ ሲጠቀስ የሚኖረውን

"ህልም አለኝ" የተሰኘ ንግግሩን አሰማ፡፡ የዚህን ንግግር ኃያልነትና ጥልቀት ለመረዳት ንግግሩ የተደረገበትን ዘመን ታሪክ መለስ ብሎ መቃኘት ያስፈልጋል፡፡ ጊዜው ሩቅ አይደለም - ማርቲን ሉተር ኪንግ በአደባባይ ለጥቁሮች ጥላቻ ባላቸው ነጮች ከተገደለ እንኳን ገና ሃምሳ ዓመት መሙላቱ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ ቅሪቶቹ በተለያየ መንገድ የሚንፀባረቁት በነጮችና በጥቁሮች መካከል የሚደረግ አድልዎ ማርቲን ሉተር ኪንግና መሰሎቹ በኖሩበት ዘመን ህጋዊ ሽፋን ያገኘ ድርጊት ነበር፡፡ ጥቁሮች በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባው የሰውነትና የዜግነት መብቶች ተነፍገዋቸው ነበር፡፡

ጥቁሮች :-

- ከነጮች ጋር በአንድ ት/ቤት የመማር፣ ምግብ ቤት ፣ መፀዳጃ ቤት፣ የህዝብ ትራንስፖርት የመሳሰሉትን መጠቀም አይፈቀድላቸውም ነበር

- በፖለቲካዊ ምርጫ በመምረጥም ሆነ በመመረጥ መሳተፍ አይችሉም ነበር፡፡

እነዚህ በአደባባይ ከሚደረጉት መዋቅራዊ መድልዎች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው፡፡ በነጭ ግለሰቦች የሚፈፀሙ ፀያፍ የአድልዎና የጥላቻ ተግባራት ከዝርዝር በላይ ናቸው፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርና የትግል አጋሮቹ ይህ ሰው በተፈጥሮው ሰው ስለሆነ ብቻ ሊያገኘው የሚገባውን የተፈጥሮ መብት ጨምሮ በአገሪቱ ህገ-መንግስት (እነርሱ የሪፐብሊኩ መስራች አባቶች (Founding Fathers) ብለው በሚጠሯቸው ግለሰቦች) የተፃፉትን መርሆች የሚቃረን መዋቅራዊም ሆነ ግለሰባዊ አድልዎ ኃይል ያልተቀላቀለበት አመፅ (Non-Violent Protest) በሆነ የትግል መንገድ ለማስቀረት እንቅስቃሴ ጀመሩ፡፡

ምንም እንኳን ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርና መሰሎቹ አመፅ-አልባ የትግል ስልትን ቢመርጡም እነርሱ የሚታገሉት የነጮችን የበላይነት የሚያራምደው መዋቅራዊ ስርዓትም ሆነ ግለሰቦች ይህን አመፅ-አልባ ትግል ለማስቀረት የተከተሉት መንገድ ፍፁም ተቃራኒ የሆነ ነበር፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርን ጨምሮ በዚህ አመፅ-አልባ ትግል ውስጥ የተሳተፉት ጥቁሮች ተደብድበዋል፣ ታስረዋል ተገድለዋል፡፡

ዛሬም ድረስ መዋቅራዊ ዘረኝነት (Systemic Racism) በአሜሪካ ጣጣው ያበቃ አይመስልም፡፡ በየግዛቶቹ ከዘረኝነት ጋር የተያያዙ አመፆችና ግድያዎች የየዕለት ዜና ዘገባዎች መሆናቸው አላበቃም፡፡

ያኔ ላይ ቆመው የወደፊቷ አሜሪካ የዘር መድልዎ ጭቆናና መብት አልባነት የሌለባት እኩልነት የሰፈነባት ሀገር እንደምትሆን ተመኙ፡፡ – "ሕልም አለኝ" አሉ፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርና አጋሮቹ ይህንን ጥቁሮቹን ከሰውነትና ከዜግነት በታች ያደረጋቸውን ስርዓት ለማስቀረት አመፁ፡፡ አንዱ የአመፁ መገለጫ የአደባባይ ሰልፍ ማድረግ ነውና በሀገሪቱ ዋና ከተማ በዋሽንግተን ዲ.ሲ አደባባይ ብዙ ሺዎች ሆነው ተሰለፉ፡፡ በዚህ የ1963 እ.ኤ.አ. የአደባባይ ሰልፍ ላይ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር "ህልም አለኝ" የተሰኘ ዝነኛ ንግግሩን አሰማ፡፡ ኪንግ እስከ 300 ሺህ የሚደርሱ ሰዎች በተካፈሉበት በዋሽንግተኑ ሠልፍ ያደረጉት ንግግር የትንቢት ያህል ተቆጥሮላቸዋል፡፡

በዚያ ንግግራቸው አፍሪካ አሜሪካውያን ከባርነት ነፃ ካወጣቸው አዋጅ 100 ዓመት በኋላም ነፃ እንዳልሆኑ አነሱ፡፡

በዚህ ንግግሩ ላይ እንዲህ አለ " ... ወደ ሀገሪቱ ዋና ከተማ የመጣነው የተሰጠንን ቼክ ልንመነዝር ነው፡፡ የሪፐብሊኩ መስራቾች አንፀባራቂ የሆኑትን ህገ-መንግስት (Constitution)ና የነፃነት አዋጅ (Declaration of Independence) በፃፉ ጊዜ ሁሉም አሜሪካዊ ወራሽ የሚሆንበትን የቃል-ኪዳን ሰነድ (Promissory Note) ነው የሰጡን፡፡ ... ይሁን እንጂ አሜሪካ ለጥቁር ህዝቦቿ 'በቂ ስንቅ የለውም' የሚል ማህተም የተረገጠበት 'ደረቅ ቼክ' ሰጥታቸዋለች፡፡ ነገር ግን የፍትህ ባንክ ከስሯል ብለን ማመን አንፈልግም፡፡ በዚህ ሀገር ታላቅ የመጠቀም ዕድል ካዝና (Opportunity Vault) ውስጥ በቂ የሆነ ሀብት የለም ብለን አናምንም፡፡ ስለሆነም ዛሬ የነፃነትን ሀብትና የፍትህን ዋስትና የሚሰጠንን ይህንን ቼክ ልንመነዝር መጥተናል፡፡"

ምንም እንኳን ይህ የደረቅ ቼክ ይመንዘርልን ጥያቄ የማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርን ህይወት ጨምሮ የብዙ ሰዎችን ህይወት ያሳጣ ቢሆንም ከግማሽ በላይ የሚሆነው ተመንዝሯል፡፡ ዛሬ ጥቁሮች :-

- የመመረጥና የመምረጥ

- ከነጮች ጋር በአንድ ት/ቤት የመማር፣ ምግብ ቤት ፣ መፀዳጃ ቤት፣ የህዝብ ትራንስፖርት የመሳሰሉትን የመጠቀም መብት አላቸው።

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ያልተመነዘሩ ቀሪ የቼኩ ስንቆች አሉ፡፡ በግለሰብና በመዋቅራዊ ስርዓት የሚደረጉ መድሎዎች አሁንም አላቋረጡም፡፡ መሳሪያ ያልታጠቁ ጥቁሮች በታጠቁ ፖሊሶች ይገደላሉ፡፡ ጥቁሮች ከነጮቹ የበለጠ በአነስተኛ የህግ መተላለፍ ጥፋቶች የረዥም ዓመታት አሊያም የዕድሜ ልክ እስራት ይፈረድባቸዋል፡፡ በቅርቡ እንኳን በስታርባክስ የቡና መሸጫ ሰው ለመጠበቅ የገቡ ሁለት ጥቁሮች ፖሊስ ተጠርቶ እንዲታሰሩ ተደርጓል፡፡ (ምንም እንኳን በኋላ የስታርባክስ ዋና ስራ አስፈፃሚ በይፋ ይቅርታ ቢጠይቅም) ይህ አይነቱ አድልዎ BLM (Black Lives Matter) የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

በየትኛውም የዓለም ክፍል ከሚደረጉ ኃይል ካልተቀላቀለባቸው የአመፅ ታሪኮች እንደ ፋኖ ከሚጠቀሱ ባለታሪከኞች መካከል ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየርና አጋሮቹ የሆኑበት ዋነኛው ምክንያት የትግላቸው መነሻ ሰው በቆዳ ቀለሙ በማህበራዊ ህይወቱና በፖለቲካዊ ስልጣን ልዩነት የተነሳ አድልዎ ሳይደረግበት የሰውነት መብቱ ሊከበርለት ይገባል የሚል መሰረታዊ መርሆ በመያዛቸው ነው፡፡

በኢኮኖሚ ያደገም ሆነ ያላደገ ሀገርን የሚመራ ግለሰብም ሆነ ቡድን የዜጎችን ሰብዓዊና የዜግነት መብታቸውን ለማክበር ዘር፣ ሃይማኖት፣ ባህል ልማድና የቆዳ ቀለምን ለአስተዳደራዊም ሆነ ለፖለቲካዊ ጥቅምም ቢሆን መሰረት ሊያደርግ አይገባም፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ "የሕልም አለኝ" አላማቸውን ለማሳካት ያደረጉት ጥረታቸው ዕውቅናው ገዝፎላቸው ከዋሽንግተኑ ሰልፍ ጥቂት ወራት በኋላ የኖቤል የሰላም ሽልማትን አሸነፉ፡፡

የመብት ሙግቱ ማርቲን ሉተር ኪንግን ከሕልም አለኝ ንግግራቸው ሦስት ዓመታት በኋላ በተፈፀማባቸው ፖለቲካዊ ግድያ ሕይወታቸውን አጡ፡፡ ሕልማቸው ግን በቀድሞው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ለዋይት ሐውስ መብቃት ፍቺ አግኝቷል፡፡

ይሄም ሆኖ በምድረ አሜሪካ ይሄ የዘር ጉዳይ አነጋጋሪነቱ አሁንም ድረስ ያልተቋጨ ሆኖ ይገኛል፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን ኣቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

ኬ
ላ

ሕግ

# የጥላቻ ንግግር ዐዋጁ ሐሳብን ከመግለጽ ነጻነት ገደብ መለኪያዎች አንጻር ሲፈተሽ!

ጥበቡ ጎ.

## ለመነሻ

በቅርቡ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የጥላቻ ንግግር እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ስለመቆጣጠር የሚደነግግ ዐዋጅ ማውጣቱ ይታወሳል። ዐዋጁ ከዝግጅት ሒደቱ አንስቶ የበርካቶችን ድጋፍና ነቀፌታ ማስተናገዱም አይዘነጋም። በርካቶች ዐዋጁ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ላይ አግባብ ያልሆነ ገደብ የሚጥል፣ መንግሥት የዜጎችን ድምጽ ለማፈንና በፍርሃት ለመሸበብ ያዘጋጀው እንደሆነ ይሞግታሉ። ከዚህም አለፍ ሲል ከአሁን ቀደም  በጸረ-ሽብር ዐዋጁ እንደሆነው የዜጎችን ሐሳብን የመግለጽ እና መረጃ የማስተላለፍ ነጻነት እጅጉን የሚጋፋና በብዙ ኢትዮጵያውያን ላይ ሲደረግ የነበረው ዓይነተ-ብዙ ግፍ እንዳይደገም በመፍራት የጥላቻ ንግግር ዐዋጁ የጸረ-ሽብር ሕጉ ሁለተኛ መልክ ነው በማለት አምርረው ተቃውመውታል።

ሌሎች በበኩላቸው በተለይም ሐገራችን ኢትዮጵያ ላለፉት ሦስት እና አራት አመታት እያስተናገደች ባለችው ፖለቲካዊ ለውጥ መግፍኤነት ግለሰቦችን እና የተለያዩ የማኅበረሰብ ቡድኖችን ዓላማ ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮች መስፋፋት፣ የተዛቡና ሐሰተኛ የሆኑ መረጃዎች ስርጭት እና የመሳሰሉትን ወቅታዊ ችግሮች በመጥቀስ የዐዋጁን መውጣት ደግፈው ሲከራከሩ ይሰማል።

የሆነው ሆኖ ዐዋጁ ከበርካታ ውዝግብ እና ንትርክ በኋላ በተለይም የሰብዓዊ መብቶች መከበር እና መጠበቅ ላይ የሚሰሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጥረት ታክሎበት መጀመሪያ ከተዘጋጀው ረቂቅ ሰነድ በተሻለ ለንግግርና ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት የተሻለ ነጻነት በሚሰጥ መልኩ ተዘጋጅቶ ጸድቋል። ነገር ግን አሁንም ቢሆን እንዲካተቱ ምክረ-ሐሳብ የተሰጡባቸው ነጥቦች አለመካተታቸው እና ከዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች መለኪያ አንጻር የሚታዩ ክፍተቶች መኖራቸው በዚህ ዐዋጅ የተነሳ ሊመጣ የሚችለው አደጋ በጣም አሳሳቢ ነው።

በተለይም እንደ ሐገር በመጪዎቹ ጊዜያት የምናስተናግደው የጠቅላላ ሕዝባዊ ምርጫ ሒደት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉትን አደጋዎች ከግምት በማስገባት በዐዋጁ አፈጻጸም ላይ በርካታ ውይይቶች ሊደረጉ ይገባል። ከሰሞኑም የተከሰቱት ሁኔታዎች ከማህበራዊ ሚዲያ ሆይ ሆይታ በዘለለ መሬት ላይ ሊሰሩ የሚገባቸው በርካታ ቁም ነገሮች መኖራቸውን ልብ ማለት ይገባል።

ከዚህ ተነስተን በዚህ ወር የኬላ አምዳችን ላይ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣውን ዐዋጅ ድንጋጌዎች ሐሳብን የመግለፅ ነጻነት ላይ የሚኖሩትን ገደቦች ምክንያታዊ እና ተቀነባይት እንዲኖራቸው ለማስቻል በዓለም አቀፍ ሕጎች ዘንድ ከተቀመጡት ባለ-ሦስት እርከን መለኪያዎች (Three-Part Test) አንጻር እንመለከታለን።

መልካም ጊዜ!

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 29/6 ላይ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት የወጣቶችን ደህነነት፣ የሰውን ክብር እና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል የሐሳብና መረጃ የማግኘት ነጻነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርሕ ላይ ተመሥርተው በሚወጡ ሕጎች መሰረት ገደብ ሊጣልበት እንደሚችል ይደነግጋል። ዓለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነትም የሌሎችን መብትና ክብር ለመጠበቅ፣ ብሔራዊ ደህንነትን ወይም የሕዝብን መረጋጋት ወይም የሕዝብን ጤንነትና ሞራል ለመጠበቅ ሲባል የሰዎችን ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ሊገደብ እንደሚችል በአንቀጽ 19/3 ስር አስቀምጧል። ሕጉ ይሄን ይበል እንጂ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ላይ የሚጣል ገደብ እጅግ ጥንቃቄ የሚሻና በቀጭን መስመር የተከለለ መሆን እንደሚኖርበት ዓለም አቀፉ የሕግ ፍልስፍና (Jurisprudence) ያስረዳል። ለዚህም ሲባል በልማድ የዳበሩት ሦስቱ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ገደብ መፈተሻ መለኪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

-1-

የመጀመሪያው ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ላይ የተቀመጠው ገደብ በሕግ የተደነገገ (Prescribed by Law) መሆን እንደሚገባው የሚያስረዳው ነው። ይህም ሲባል ሐሳብን በመግለጽ ነፃነት እና እዚህ መብት ላይ ሊጣል በተፈለገው ገደብ መሐል ያለው ርቀት ተገቢው ሕጋዊ መስመር ሊበጅለት እንደሚገባ የሚገልጽ መለኪያ ነው። አንድ ሰው ሐሳብን የመግለጽ ነጻነቱ ገደብ የማይኖረው የት ድረስ መሆኑን እና ከየት ወዲያ የሕዝብን ወይም የግለሰቦችን ደህንነት የሚጎዳ ንግግር ማድረጉን ወይም ሌላ ሕጉ የሚያስቀምጠውን መስመር በመተላለፉ ቅጣት እንደሚጣልበት የሚያሳይ መሆን ይገባዋል። ከዚህ በተጓዳኝ ሕጉ መሠረታዊ የሕግ የበላይነት መርሆዎችን ለሟሟላት የሚረዱትን እንደ ተደራሽነት፣ ግልጽና ትክክለኝነት እንዲሁም ተገማችነትን የመሳሰሉትን ሁኔታዎች በበቂ ሁኔታ ያሟላ መሆን ይጠበቅበታል።

አዲሱ የጸረ-ጥላቻ ንግግር ዐዋጅ ከዚህ አንጻር ጥቂት የማይባሉ ክፍተቶች አሉት። የመጀመሪያው በአንቀጽ 6/1/ሐ ስር በዐዋጁ ከተቀመጡት ገደቦች ነጻ የሆኑትን የንግግር ወይም ሐሳብን የማስተላለፊያ መንገዶች አንዱ ጥበባዊ ስራዎችን ወይም ክንውኖችን ወይም ሌላ ዓይነት መግለጫዎችን የተመለከቱ ከሆነ የሚለው፤ በተለይም “ሌላ ዓይነት መግለጫዎችን” የሚለው አገላለፅ በግልጽ ገደቡ የሚታወቅ አይደለም። ሌላኛው የጥላቻ ንግግሮች ክልክል ስለመሆናቸው በሚገልጸው አንቀፅ 4 ስር እንዲህ ዓይነቶቹን ንግግሮች በብሮድካስት፣ በሕትመት፣ ወይም በማሕበራዊ ሚዲያ ማስተላለፍ የማይቻል መሆኑን ይገልጻል። ሆኖም ዘመኑ ባፈራቸው የቴክኖሎጂ እድገቶች ሳቢያ በብሮድካስትም ሆነ በማሕበራዊ ሚዲያዎች ላይ በቀጥታ የሚተላለፉ ዝግጅቶች በመኖራቸው በዚህ ወቅት ኃላፊነቱን ማን ሊወስድ እንደሚችል በግልጽ የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ ዐዋጁ በመናገር ነጻነት ላይ ያስቀመጠውን ገደብ በሕግ አግባብ ደንግጓል ለማለት ያስቸግራል።

-2-

ሁለተኛው መለኪያ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ላይ የተቀመጠው ገደብ በሕግ የታወቀ ወይም ቅቡልነት ያለው ዓላማ (Legitimate Aim) ይዟል ወይ የሚለው ነው። ይህም ሲባል ገደቡ መነሻ ያደረጋቸው አመክንዮዎች ሕጋዊ ቅቡልነት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል ማለት ነው። እንደ የሐገርን ወይም የሕዝብን ደሕንነት ለመጠበቅ፣ ወንጀልን ለመከላከል፣ የሕዝብን ጤና እና ሞራል ለመጠበቅ የመሳሰሉት ምክንያቶች ሐሳብ የመግለጽ ነፃነትን መገደብ የሚያስገኘው ጥቅም ወይም የሚያስከብረው ፍላጎት ያለ በመሆኑ ሕጋዊ ተቀባይነት ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ሕጉ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን ለመገደብ ያነሳሱትን ገፊ ምክንያቶች አንድ ሁለት ብሎ መዘርዘር ይኖርበታል፡፡

ከዚህ አንጻር በግሌ ዐዋጁ በሐሰተኛ መረጃዎች እና በተዛቡ ወይም ጥላቻን ባነገቡ ንግግሮች የተነሳ የሚደርሰው ጥፋት ወይም የሰብዓዊ መብቶች ቀውስ ለመከላከል የሚያስችል ቅቡል አመክንዮ እንዳለው አምናለሁ። ነገር ግን የዐዋጁ ድንጋጌዎች እና የሕጉን መንፈስ ለመረዳት የሚጠቅመን የመግቢያው ክፍል ለሁሉም ግልጽ በሆነ ቋንቋ ስለመገለጻቸው እጠራጠራለሁ፡፡

-3-

ሦስተኛው እና የመጨረሻው ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ላይ የሚጣሉት ገደቦች አንድ ዲሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ወይ (Are they necessary in a democratic society?) የሚለው ነው። ይህ እንግዲህ በዚህ ነጻነት ላይ የምናስቀምጠው ገደብ ማሳካት ለምንፈልገው ማኅበረሰባዊ ፍላጎት መሳካት አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር የግድ አስፈላጊ ነው ወይ የሚለውን ጥያቄ በአዎንታዊ መንገድ የሚመልስ መሆን የሚጠበቅበት መለኪያ ነው።

ከዚህ አንጻር አዲሱ የጥላቻ ንግግር ዐዋጅ ከሕግ በፊት ማኅበረሰባዊ ልማት ያስፈልጋል የሚለውን የሕግ ፍልስምና ተቃርኖ የወጣ ሆኖ እናገኘዋለን። በመሠረቱ ሕግ ማውጣቱ ብቻውን በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ያስችላል ማለት አይደለም። ከዚያ በፊት ለአንድ ማኅበረሰብ ሕልውና መሠረታዊ ለሆኑት እንደ ቤተሰብ፣ ኃይማኖት፣ ትምህርት፣ ኢኮኖሚ እና መንግስታዊ ስርዓት የመሳሰሉትን ተቋማት በማጠናከር ችግሩን ለመፍታት መጣር ያስፈልጋል። እነዚህን ሳናጠናክር ችግሩን ለመፍታት ሕግ ማውጣት ልምጩን ከካሮቱ ፊት ማስቀደም ይሆንና የከፋ ውስብስቦሽ ውስጥ ለመግባት ራሳችንን ማመቻቸት ይሆናል። ምክንያቱም ለማኅበረሰባዊ ችግሮቻችን በሙሉ ሕግና ዱላ ይዘን መነሳት ለህመሞቻችን ሁሉ የራስ ምታት ማስታገሻ እንደመዋጥ ያለ ማስታገስ ወይም/እና ማባባስ ሊሆን ስለሚችል ቅድሚያ መሰራት ያለበትን መስራት አስፈላጊ ነው።

ከዚህ አንጻር አዲሱን ዐዋጅ ለማውጣት መነሻ የሆኑ ጉዳዮችን በሕግ መፍታት ተገቢ ነው ወይስ አይደለም፤ ይህ ሕግ እንደ ሐገር መፍጠር ለምናስበው አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ምን ያህል ጠቃሚ ነው የሚለው በደንብ ተፈትሾ መውጣት ሲገባው በችኮላ እንዲጸድቅ መሆኑ አግባብ አይደለም፡፡ አሁን ግን ቢያንስ አፈጻጸሙ ላይ ከላይ የጠቀስናቸው ተቋማት የሚኖራቸውን ድርሻ በመለየት እስከአሁን እንዳስተናገድናቸው ዓይነት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዳናይ የሚያደርግ ሥራ ሊሰሩ ይገባል፡፡

.../...

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

# ቀለም

//

## የካቲት 12 እና በኢትዮጵያውያን ላይ የተፈፀመ ዘግናኝ ጭፍጨፋ



ምስል ፋሺስት ኢጣልያ በአዲስ አበባ የፀመው ጭፍጨፋን የሚያሳይና የመታሰቢያ ሀውልት

ዳን ዖርጋ

### ወርሀ የካቲት ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው

እንደ አጋጣሚ ሆኖ አንዳንድ ወራትና ቀናት የግለሰቦችንና የአገሮች ታሪክ ላይ ጉልህ ሚና በማስተናገዳቸው በታሪክ ማህደር ሰፍረው በትውልድ ሲተረኩ ይኖራሉ።

እንደ ሀገር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ወርኃ የካቲትን የመሰለ በየታሪክ ህዳጉ የኢትዮጵን ቅርፅና ሁኔታ የወሰነ ወር የለም ለማለት ያስደፍራል።

ወርኃ የካቲት በኢትዮጵያ የመካከለኛው ዘመን ዝነኛውን ንጉስ አጼ ሠርፀድንግልን፣ “የዘመናዊት ኢትዮጵያ ጠንሳሽ ናቸው” የሚባሉትን አጼ ቴዎድሮስንና ንግስት ዘውዲቱን ወደ ስልጣን ያመጣ ወር ነው።

ከጀግኖችም ውስጥ እቴጌ ጣይቱን፣ ንጉስ ወልደጊዮርጊስን፣ ራስ ደስታ ዳምጠውን፣ ራስ አሉላ እንግዳንና ሌሎች ብሔራዊ የጦር ጀግኖች ያረፉበት ታሪካዊ ወር በመሆን በታሪክ ድርሳናት ተጠቅሷል።

በሌላ በኩል በኪነ ጥበብ መስክ ደግሞ ወርኅ የካቲትን ያህል የሞት ዶፍ የወረደበት ወቅት እንደሌለ ብዙዎቹ ያስማማል። ለአብነትም ብዕረኛ አቤ ጉበኛ እረፍት የካቲት 2፣ ስብሐት ገብረ እግዚአብሄር የካቲት 12፣ ጸጋዬ ገብረመድህን የካረቲት 18፣ ማሞ ውድነህ የካቲት 23፣ እንዲሁም ተወዳጁ ደራሲና ጋዜጠኛ በዓሉ ግርማ እንደወጣ የቀረው የካቲት 24 እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

በፋሽስት ወራሪው ጣልያን በ1929 ዓ.ም ከ30 ሺህ በላይ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በጅምላ በአካፋና በዶማ በግፍ የተጨፈጨፉትም በዚሁ ወር በካቲት 12 ነው።

በ1928ቱ የጣሊያን ወረራ ወቅት በሽሬ፣ በተንቤንና በተለያዩ የጦር ሜዳዎች በአለም አቀፍ ህግ የተከለከለ መርዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ ተርከፍክፎ እንዲቃጠሉ መደረጉም የታሪክ ድርሳናት እማኝ ናቸው።

በሌላ አስደናቂ የታሪክ ወቅት ደግሞ ኢትዮጵያ በወርኃ የካቲት ለጥቁር ህዝቦች ቀንዲል የሆነውን የጣሊያን ወረራን በአድዋ፣ የግብጽን ወረራ በጉራ፣ የሶማሊያ ጦርነትን ደግሞ በካራማራ ድል የተቀዳጀችበት ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሰፋ ያለ ስፍራ ይዘው ከተቀመጡ ክስተቶች መካከል ከጣሊያን ጋር የተደረጉ ሁለት ጦርነቶች ዋነኞቹ ናቸው። ኢትዮጵያ በነጮች ዐይን ውስጥ ብትወድቅም ከክንዳቸው በታች ልትሆን አልወደደችምና። ቀዳሚው የአፍሪካውያን ኩራት የሆነው የዓድዋ ድል ሲሆን፤ ሁለተኛው ይኸኛው የየካቲት 12 መታሰቢያ በዓል ነው።

ይህ የአምስት ዓመታቱ የጦርነት ታሪክ፤ ኢትዮጵያ እንደ አገር ብዙ ፈተና ያየችበት ወቅት ነው። ጣሊያን ከዓድዋ ጦርነት በኋላ በሚገባ የተዘጋጀችበት ወቅት ነበር የረሁንና ኢትዮጵያ ደግሞ የለውጥ ሽግግር ላይ በመሆኗ ዝግጁ ያልነበረችበት፣ መሪዋም የዓለም አገራትን ለመማፀን ስደት የወጡበትና ሕዝብን አንድ አድርጎ የሚመራ መሪ ያልነበረበት እንዲሁም የዓለም መንግሥታት ሁሉ ጀርባቸውን በኢትዮጵያ ላይ ያዞሩበት ወቅት በመሆኑ በጣም ፈታኝ ወቅት ነበር።

የኢትዮጵያውያን የአርበኝነት ትግል ለአገር የነጻነት፣ ክብርና ለሉዋላዊነት የተከፈለ መስዋትነት ነው፡፡ ይህም ማለት ኢትዮጵያውያን ለመብታቸውና ለሰብዓዊ ክብራቸው የሚቆሙ ዜጎች መሆናቸውን በግልፅ ያሳያል ይህንንም በተደጋጋሚ ለዓለም አስመስክረዋል፡፡

አምስቱ ዓመታት የጦርነትና የመከራ ጊዜ ብቻ ብሎ ከመናገር ይልቅ የሰብዓዊ ክብርን፣ ባርነትን የመቃወሚያ የትግል ወቅት ማለቱ ሳይቀል አይቀርም። በበኩሌ ይህን የምለው ከምናነባቸው ታሪኮችና ከዛም ካገኘነው ክብር አንፃር፤ ጣሊያኖች በኢትዮጵያ ላይ ካደረጉትና ከፈጸሙት ግፍ በላይ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ታሪክ[1] ለአገራቸው ስለሰሩ ነው። ታዲያ በአምስቱ ዓመታት ውስጥ የሚያባራ የማይመስል መከራን ኢትዮጵያውያን በገዛ አገራቸው ላይ ስለነጻነታቸውና ክብራቸው በመሟገታቸውና ባርነትን በመጥላታቸው ብቻ አስከፊ ጭፍጨፋ ተፈፅሞባቸዋል።

ዘንድሮም 83ኛው ዝክረ በዓል ማለትም የካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ ቀን በግፍ የተጨፈጨፉትን ከ30.000ሺ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን ለመዘከር በስፋት ተከብሯል፡፡ ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ በጣሊያን የተፈፀመባትን የዘርማጥፋት በማናጨውም የዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት አቅርባ አታውቅም ይሁንና ይህ ስራ አስከ ዛሬ አይሰራ እንጂ ለወደፊት ሰነዶችንና ተቋማትን በአግባቡ በማደራጀት ይህንን ክስ ማቅረብ የሚቻል ስለሆነ ሁሉም ኢትዮጵውያን በዚህ ረገድ ትብብርና ርብርብ እንዲያደርጉ በዚህ አጋጣሚ መግለፅ እወዳለሁ፡፡

ቸር ያሰማን!

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

---

1 ማጣቀሻ መጻህፍት

- የጥላሁን ጣሰው (የኢትዮጵያና የጣሊያን ሁለተኛው ጦርነት)
- ጳውሎስ ኞኞ (የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት)
- ፐ/ር ላፒሶ ደነቦ (የኢትዮጵያ ታሪክ)
- ግዛው ዘውዴ (በዝክረ አርበኝነት እና የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማኅበር አጭር ታሪክ)
- ቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ (ቀሪን ገረመው)